የአዋቂዎች ጥበቃ አገልግሎቶች (APS) ምርመራዎች መረጃ በበራሪ ወረቀት

Adult Protective Services (APS) Investigations Fact Sheet

የአዋቂዎች ጥበቃ አገልግሎት (APS) እርስዎ አቅመ-ደካማ አዛውንትን በድለዋል፣ ጥለው ጠፍተዋል፣ ገንዘባቸውን መዝብረዋል ወይም ቸል ብለዋል ተብሎ የቀረበን ሪፖርት እየመረመረ ነው። ይህ ሰነድ የምርመራ ሂደቱን፣ መብቶችዎን እና ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎችን ያሳውቆታል። እንደ ምርመራው አካል APS መዝገቦችን ይመረምራል እንዲሁም ደግሞ ስለክሱ (ክሶቹ) ከሰዎች ጋር ቃለ-መጠይቅ ያደርጋል።

የምርመራው ውጤት በእርስዎ ላይ ከበድ ያለ ጫና ልኖረው ይችላል።
እባክዎን ይህንን በጥንቃቄ ያንብቡ።

ለእርስዎ ጉዳይ የተመደቡ መርማሪ፡-
በሚከተለው ይገኛሉ፡-

ምን ዓይነት መብቶች አሉኝ?

- በቃለ-መጠይቁ ጊዜ ሦስተኛ ወገን (እንደ ጓደኛ፣ ጠበቃ፣ የዩኒዬን ተወካይ፣ የቤተሰብ አባል ወይም አሳዳጊ) ከእርስዎ ጋር እንሆኑ ለማድረግ መብት አለዎት።
- እንግሊዚኛ የመጀመሪያ ቋንቋ ካልሆነ ነፃ የአስተርጓሚ መብት አለዎት (APS የቤተሰብ አባልን እንደ አስተርጓሚ መጠቀም ስለማይፈቀድለት)።
- በቃለ-መጠይቁ ላለመሳተፍ፣ ማቋረጥ ወይም ለሌላ ጊዜ ለማስቀጠር መብት አለዎት።
- ክሱን በተመለከተ ለAPS ሰነዶችን ወይም ምስክሮችን ለማቅረብ መብት አለዎት።

APS የምርመራውን ውጤት እንዴት ያሳውቀኛል?

- APS ውሳኔ የሚሰጠው እራሱ APS በምርመራ ጊዜ በሰበሰባቸው መረጃዎች ላይ በመንተራስ ነው። APS የሚሰጣቸው የውሳኔ ዓይነቶች፡-
  - **በመረጃ የተደገፈ**፡- የቀረበው ክስ ስለመፈጠሩ የሚጠቁመው ማስረጃ ያመዝናል ለክሱ ምክንያት የሆነው ክስተት ተከስቷል
  - **በመረጃ ያልተደገፈ፡-** የቀረበው ክስ ስለመፈጠሩ የሚጠቁመው ማስረጃ ያመዝናል ለክሱ ምክንያት የሆነው ክስተት አልተከሰተም
  - **ድምዳሜ ላይ ያልተደረሰበት፡-** የቀረበው የክስ ክስተት መከሰቱን መወሰን አይችልም።
- APS የተፈጠረው ክስተት ሊሆን ከሚችለው በላይ ሆኖ ካገኘ፣ APS ዕውቅና ባለውና በፖስታ ደብዳቤ በመላክ ያሳውቅዎታል።
- APS የተፈጠረው ክስተት ሊሆን ከሚችለው በላይ ሆኖ ካላገኘ፣ APS በቃል ያሳውቆታል። APSን ቢጠይቁ ደብዳቤ ሊያቀርብልዎት ይችላል።
- APS ክስተቱ መፈጠሩን መወሰን ካልቻለ፣ APS በቃል ያሳውቅዎታል። APSን ቢጠይቁ ደብዳቤ ሊያቀርብልዎት ይችላል።
- የአዋቂዎች ጥበቃ አገልግሎት (APS) የእርስዎን የአሁኑ አድራሻ ከሌለው፣ አስፈላጊ ደብዳቤዎች እና የጊዜ ገደቦች ሊያመልጥዎ ይችላል።

በመረጃ የተደገፈ ግኝት ማለት ምን ማለት ነው?

APS የጫና/በደል፣ የመነጥል፣ የመገለል ወይም የገንዘብዎ መመዝበር ክሶች “በመረጃ መደገፉን” መሆኑን ከወሰነና በውጤቱ ካልተስማሙ ስሞታ ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ። የAPS ውሳኔ ከስሞታው ሂዴት በኋላ ከፀና፣ ስምዎ በመዝገብ ላይ እንዲኖር ይደረጋል።

በመዝገብ ላይ መሆን ማለት ተጋላጭ ከሆኑ አዛውንቶች ወይም ሕጻናት ጋር ክትትል በማያስፈልገው ግንኙነት የትም ቦታ መስራት ወይም በበጎ ፈቃደኝነት ማገልገል ላይችሉ ይችላሉ ማለት ነው። በአሁኑ ጊዜ ስምዎን ከመዝገቡ ላይ ማስወገድ/ማሰረዝ አይቻልም።

የAPS ውሳኔ መቃወም እችላለሁ?

- APS ተፈጥሮ የነበረው ክስ በመረጃ **ያልተደገፈ** ከሆነ ወይም መደምደሚያ **ከለሌው** ምንም ማድረግ አይጠበቅብዎትም።
- APS ተፈጥሮ የነበረው ክስ በመረጃ **የተደገፈ** መሆኑን ከወሰኔና የማይስማሙበት ከሆነ ለስሞታ ማመልከት ይችላሉ። የAPS ደብዳቤ እንዲያውቁ ያደርጋል።

የዲፓርትመንቱ የማሳወቂያ ደብዳቤ በፖስታ ከደረሰዎ ወይም በእጅ ከደረሰዎ፣ በማንኛውም ቀድሞ በደረሰ በቀን አቆጣጠር በ 30 ላይ እስክ 5፡00 p.m. ድረስ አቤቱታ እንዲሰማ መጠየቅ ይችላሉ።

ለተጨማሪ መረጃ

ስለAPS ተጨማሪ መረጃ ከ https://www.dshs.wa.gov/altsa/adult-protective-services-aps ማግኘት ይችላሉ።